# OFFICE OF CONSUMER PROTECTION

**በዓላት የደስታን ጊዜ ብቻ አያመጡም ከዛ በላይ ... አጭበርባሪዎችንም ይጋብዛሉ እንጂ**

ኖቬምበር 2 2020

በዓላቱ እየደረሱ ነው :: በወቅቱ ወረርሽኝ በሽታ ሰበብ የተለመዱ የማጭበርበሪያ ዘዴዎች መልካቸውን ቀይረው እንደመጡት ሁሉ፤ በበዓላትም ወቅት ብዙ ወንጀለኞችም ብቅ ይላሉ። በበአላት ሰሞን ባዶ የስጦታ ካርዶች ፣ የሐሰት በጎ አድራጎት ልመናዎች ፣ የሳይበር ጥቃቶች እና ከደጅዎ ላይ የፖስታ ፓኬጆችን መስረቅ አዲስ ነገር አይደለም። ነገር ግን ሸማቾች ዘንድሮ በ2020 በተከሰተው ወረርሽኝ ጭንቀት የተነሳ፤ በኢንተርኔት በሚደረጉ ግብይቶች እና ንግግሮች ላይ በጣም ለመተማመን በመገደዳቸው በቀላሉ በአጭበርባሪዎች ወጥመድ ሊወድቁ ይችላሉ። በዚህ የበዓል ወቅት ደህንነትዎን ለመጠበቅ የሚረዱ ጥቆማዎች እነሆ.

## Online Shopping የመስመር ላይ ግብይት

በፌዴራል ንግድ ኮሚሽን መሠረት ፣ የግብይት ክፍያዎችን በክሬድት ካርድ መፈጸም የተሻለ የደህንነት ዋስትና ያለው ነው። ለአብዛኛዎቹ የኦንላይን ግዢዎች ተጨማሪ የደህንነት ጥበቃዎችን ይሰጣልና። በተጨማሪም፤ በክሬዲት ካርድ ግዥዎች ዙርያ የሚነሱ ክርክሮችን ማስተናገጃ፤ የተገዙ ነገሮችን የማስመለሻ ወይም የማስቀየሪያ አሰራሮች አሉት። የዴቢት ካርዶች፤ የቪዛ ወይም ማስተር ካርድ አርማ ያላቸው እንኳን ቢሆኑ እንደ ክሬዲት ካርዶች ያለ መከላከያዎችን እና የክርክር ማስተናገጃ አሰራሮች የሏቸውም።




ግዢዎችን የፈጸሙት በክርግስሊስት ፣ በፌስቡክ ፣ በሌትጎ ወይም በሌላ ሶስተኛ ወገን የገበያ መስመሮች ላይ ቢሆን እንኳን፤ አጭበርባሪዎቹም እንዲሁ ለማጭበርበር እነዚሁኑ መድረኮች እንደሚጠቀሙ አይዘንጉ። ወንጀለኞች በነጻ የሚገኙ ፎቶዎችን ወይም ከሌላ እውነተኛ ግብይቶች ላይ ፎቶዎችን ወስደው፣ የእውን የሌሉ ሸቀጦችን እስከመሸጥ እና ኪራዮች እስከማከራየት ይደርሳሉ። የሚገዙበት ዋጋ እውነት የማይመስል ከሆነ፤ ክፍያ ከመፈጸምዎ በፊትም የሚገዙትን ነገር ማየት የማይችሉ ከሆነ፤ በአጭበርባሪዎች

*Ensuring Integrity in our Marketplace*

If you have been a victim of a scam, or if you have any disputes over a merchant's activities, please contact the Office of Consumer Protection.

100 Maryland Avenue
Suite 3600
Rockville, MD 20850
Main: 240.777.3636
Tip Line: 240.777.3681
Fax: 240.777.3768
Consumer@MontgomeryCountyMD.gov

You can also **file a complaint** online by clicking **HERE**

ወጥመድ ውስጥ እየወደቁ እንደሆነ የሚያሳይ ጥሩ ምልክት ነው። እርስዎ ሻጭ ከሆኑ ደግሞ ገዥው ክፍያውን በቼክ ለመፈጸም ሊጠይቅ እና ከጠየቁት ዋጋ በላይ እከፍላለሁ ብሎ ሊስማማ ይችላል። የዚህ ማጭበርበር ዋናው አላማ በኋላ የገንዘብ ተመላሽ በመጠየቅ እርስዎ ክፍያውን በእውነተኛ ቼክ ጽፈው እንዲሰጡት ለማድረግ ነው። ይህም የቼክ አጭበርባሪዎች አንዱ ዘዴ ነው።


በመጨረሻም ፣ በዚህ ዓመት ገንኖ የታየው በሃሰተኛ የችርቻሮ ድረገጾች ላይ የሀሰት እቃዎችን ሽያጭ የሚያስተዋውቁ የንግድ ማስታወቂያዎች ናቸው። አብዛኞቹ ሾፒፋይ እና ሌሎች የማህበራዊ ድረገጾችን መድረክ ይጠቀማሉ። እነዚህ ነጋዴዎች ሐሰተኛ እቃዎችን ይሸጣሉ ወይም አለን ያሉት የሚሸጥ ዕቃዎች የሏቸውም። ባዶ እሽጎችን በመላክ የማስረጃ ሰነድ ያበጃሉ፤ በዚህም ከደንበኞች እና ባንኮች የሚነሱባቸውን ክርክሮች ይሞግታሉ። እንደ ፎርብስ መጽሔት ዘገባ ማጭበርበር ያለበት ግብይት አንዱ መለያ ተመሳሳይ ማስታወቂያዎችን እና ፎቶግራፎችን እና የታላቅ ቅናሽ ሽያጭ ማስታወቂያዎች ስማቸው እንግዳ የሆኑ የተለያዩ ካምፓኒዎችን ስም ይዘው መታየታቸው ነው። ለምሳሌ ፕሬዲክትፊቸር (Predictfuture) የተባለ ካምፓኒ በቅናሽ የሚሸጠውን አንድ የስፖርት መስሪያ መሳሪያ ሌላ Geoghost.store የተባለ ድረገጽ በተመሳሳይ ቅናሽ ዋጋ ሲሸጥ መገኘቱ ነው።

## Gift Cards የስጦታ ካርዶች


እነዚህ ካርዶች ስጦታዎችን ታላቅ እና ቀላል ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን የእነዚህን ካርዶች አጠቃቀም ለመከታተል አስቸጋሪ እንደሆነ በሚያውቁ ወንጀለኞች ዘንድ ተመራጭ የማጭበርበሪያ መላዎችም ናቸው። አንድ ሰው ያልተከፈሉ እዳዎችን ወይም ወርሃዊ ክፍያዎችን በስጦታ ካርዶች እንዲፈጽሙ ከጠየቀዎ ወይም ገንዘቡን በባንክ የዋየር ክፍያ እንዲያስተላልፉ መጠየቅ ከጀመረ፤ የማጭበርበር ሥራ እየተከናወነ እንዳለ የሚጠቁምዎ ቀይ ባንዲራ ነው። የስጦታ ካርዶች ሲገዙ ፣ ማሸጊያው ያልተከፈተ/ ያልተላጠ ስጦታ ካርድ መሆኑ ያረጋግጡ ወይም ማሸጊያው የካርዱን ባር ኮድ የሚያሳይ ከሆነ አይግዙ ፡፡ በ CNBC በተዘገበው የ ኤ.ኤ.አር.ፒ (AARP) የዳሰሳ ጥናት መሠረት፣ሸማቾች ከተቀበሉት ከ 5 ቱ የስጦታ ካርዶች ውስጥ 1ዱ ካርድ ባዶ ሆኖ እንዳገኙት ተናግሯል። ወንጀለኞች ባዶ ካርዶችን መዝግበው ይይዙና፤ ካርዶቹን በስጦታ የሚሰጠው ሰው ካርዱ ያለውን ገንዘብ ልክ አክቲቬት ሲያደርግ ጠብቀው ውስጡ ያለውን ገንዘብ ከመቅጽበት ይወስዱታል፤ የሚሰጠውንም የስጦታ ካርድ ለተቀባይ ከመስጠቱ በፊት ቀድመው ባዶ ሊያደርጉት ሁሉ ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪም እንደዘገበው በድረገጽ ላይ በሚደረጉ ጨረታዎች የሚሸጡ አብዛኛዎቹ የስጦታ ካርዶች የተሰረቁ ካርዶች ናቸው። በዚህ ጉዳይ ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ስለ ስጦታ ካርዶች አጠቃቀም የሚያስረዳውን ድረገጽ ይጎብኙ።

## Cybersecurity የሳይበር ደህንነት

የበይነመረብ አጥማጆች እና አስመሳዮች ሐሰተኛ "የተላከልዎት እቃ ዘገየ" የሚሉ መልእክቶችን በመላክ የሳይበር ጥቃቶች የሚጀምሩበት ወቅት ነው።




ወይም ካልታወቁ ነጋዴዎች የሃሰት የኩፖን ስጦታ መልዕክት በመላክ ተደጋጋሚ ጥቃት ይሞክራሉ




እነዚህን መልእክቶች በሚገመግሙበት ጊዜ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ፡- የላኪ አድራሻ ትርጉም አለው/ትክክለኛ ነውን? የዩ ኤስ ፒ ኤስ ኢሜይል የተላከው ከ .biz ነው ወይስ .net? ማስፈንጠርያ/ሊንኩ ወደ ፌዴክስ (FedEx) የሚመራዎ መስሎ ነገር ግን የ FedEx ድረገጽ ወደማይመስል የሚወስድ ነው? በተጨማሪ አጠራጣሪ ኢሜሎች፣ ጽሑፎች ወይም የውይይት ሚዲያ ወይም ሌላ የግንኙነት መተግበሪያ መድረኮችን ማስፈንጠርያ አይጫኑ። ማስፈንጠሪያዎቹን ከተጫኑ እርስዎን በማጭበርበር ውስጥ ያሳትፉዎታል ፣ ወይም የኮምፒውተር ቫይረስ ወይም ተንኮል-አዘል ሶፍትዌር ፕሮግራም በመጫን የግል መለያ ምስጢራዊ ቁልፎችዎን እና የኢሜል መዳረሻዎችዎን በመስረቅ ወደፊት የማንነት መለያ ስርቆት ያመቻችዎታል። ለተጨማሪ በድረገጾችን ላይ ስለ በይነመረብ አጥማጆች እና አጭበርባሪዎች የሚያስተምረውን ገጽ ይጎብኙ።

## Porch Pirates የበረንዳ ወንበዴዎች

የበረንዳ ላይ ወንበዴዎች አዲሱ የስርቆት ዓይነቶች ናቸው በመደብሮች ውስጥ ሸቀጣ ሸቀጦችን ከመስረቅ ይልቅ እነዚህ ወንጀለኞች ከቤትዎ በረንዳ ላይ ይሰርቁታል። በአንድ ዘገባ መሠረት 36% የሚሆኑት ተጠቃሚዎች በ 2019 ቢያንስ አንድ የተላከላቸውን እቃ ከበረንዳቸው ላይ እንደተሰረቁ  ዘግቧል።



የበረንዳ ላይ ወንበዴን ለመዋጋት የተላኩልዎትን እሽጎች/ጥቅሎችዎን ጉዞ በድረገጽ ላይ ይከታተሉ። እሽጎች ከቤትዎ ይልቅ ወደ ሥራ ቦታ  አድራሻ እንዲላክልዎ ያድርጉ ወይም እዚያው ከመደብሩ ሄደው ለመውሰድ ይሞክሩ፣ ወይም የፊት በር ደህንነትን ካሜራ ይትከሉ፣ በረንዳዎ ላይ ቁልፍ ያለው ሳጥን ያዘጋጁ - ሌቦች ካሜራዎች ይፈራሉ፡፡ ዕቃዎች ከተሰረቁ ደግሞ በፍጥነት ለነጋዴው እና ለጭነት አቅራቢው ጉዳዩን ያስመዝግቡ።

## Mail Marauders የፖስታ ዘራፊዎች

በበአላት ወቅት ሰዎች የፖስታ ሳጥናቸውን የበዓል ፖስትካርዶችን በውስጣቸው ቼኮችን ወይም የስጦታ ካርዶች ጨምረው ለመላክ ይጠቀማሉ። በመልዕክት ሳጥኖች ላይ ያሉ ባንዲራዎች ፖስታዎችን በቀላሉ በሌቦች ሊሰረቁ እንደሚችሉ የሚያሳስቡ ማስጠንቀቂያዎች ናቸው።



ወንጀለኞች ደብዳቤዎን ይሰርቃሉ፣ “የቼክ አጣቢዎች” ቼኮች እንደገና ለራሳቸው ይጽፉታል ፣ ወይም ቼክዎ ላይ የሚያገኙትን የግል መለያዎን በመጠቀም የሐሰት ቼኮችን ያትማሉ። ፖስታዎችዎን ሲልኩ በሰማያዊው ሳጥን ውስጥ ያስቀምጡ ወይም በቀጥታ ወደ ፖስታቤት ቢሮ ወስደው ይላኩ።

## Donations ልገሳዎች

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና የበጎ አድራጎት ልገሳዎች በበዓላት ሰሞን ይጨምራሉ። የበጎ አድራጎት ድርጅት ሥጦታ ከመስጠትዎ በፊት፣ የሚለግሱለት የበጎ አድራጎት ድርጅት ህጋዊ ይሁን ወይስ አጭበርባሪ ተቋማት የሁኑ ይለዩ።  በሜሪላንድ ሀገር ግዛት ሚንስቴር/ ሴክሬተሪ ኦፍ ስቴት/ መመዝገባቸውን ያጣሩ፡፡




ከዚያ ተቋማቱ የለገሱትን ገንዘብ ለትክክለኛ ሥራ ላይ ያውሉት ወይም ተጨማሪ የስልክ ልመና አቀናባሪዎችን ለመቅጠር እየተጠቀሙበት እንደሆነ ይመርምሩ። እንዲህ አይነቱን መረጃዎች በቀላሉ የሚያገኙባቸው ድረገጾች Charity Navigator, Guidestar, Charity Watch, Give.org የመሳሰሉት ከብዙ በጥቂቱ ናቸው።

## Conclusion ማጠቃለያ

በዚህ የበዓል ወቅት ደህንነትን ለመጠበቅ ተጨማሪ ትጋት ያስፈልጋል። በተጨማሪ የበዓላት ግብይቶችን በተመለከተ፤ወይም ተዛማጅ አርዕስቶችን  ለምሳሌ የዲጂታል የክፍያ መተግባሪያዎችን ከ ክሬዲት እና ዴቢት ካርድ በበለጠ ስለመጠቀም፤ ወይም በሜሪላንድ የተገዛ እቃን የመመለስ እና የማስቀየር ህጎችን የተመለከቱ መረጃዎችን ለማግኘት እባክዎ ድረገጻችንን ይጎብኙ።